በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

ከጁላይ 21-31/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ እና

ከኦገስት 1-10 እና 11-10/2026 የሚኖረዉ የአየር ሁኔታ

ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ጁላይ 2026

አዲስ አበባ

1. እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን፣ መካከለኛዉ እና ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን ነበራቸዉ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ እና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል፡፡ በ24 ሠዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል ሀዋሳ 56.7፣ ባህር ዳር 44.4፣ 61.5፣ ኮምቦልቻ 30.4፣ ደብረ ማርቆስ 30፣ ቢሾፍቱ 35.1፣ ጎንደር 34.4፣ ጎሬ 31፣ ጅማ 37.6፣ አዴት 36፣ አይራ 47.4፣ አማን 30.5፣ አምባ ማሪያም 38.6፣ አምደወርቅ 37.6፣ አንገር ጉትን 33.2፣ 40፣ አርጆ 32.8፣ አርሲ ሮቤ 40፣ አሶሳ 62.3፣ አፅቢ 40.7፣ አይከል 52. ባቲ 65፣ ቦሬ 42፣ 36.8፣ ቡሂ 39.7፣ 34.2፣ ቡለን 40፣ 30፣ 70፣ ቻግኒ 30፣ ጨፋ 60፣ ጭፍራ 61.2፣ ጭራ 35፣ ዳሊፋጊ 38.2፣ ደበረ ብርሃን 48.3፣ ደበረ ወርቅ 44.1፣ 52.8፣ ደምቢ ዶሎ 35.2፣ ፊቼ 38.8፣ 31.6፣ 43.7፣ ፉኙዶ 80፣ ገለምሶ 34.5፣ ጊምቢ 55.4፣ 50.4፣ ጉንዶ መስቀል 35.6፣ 49.3፣ እምድብር 31.4፣ ላሊበላ 90፣ ሊሙገነት 33፣ ማጀቴ 38.4፣ ማንኩሽ 60.2፣ ማሻ 30፣ መካነሰላም 35.2፣ መተማ 44.8፣ ንፋስ መዉጫ 48.7፣ ፓዌ 32.2፣ ሰኮሩ 32፣ ሰንቃጣ 30.5፣ ሲርንቃ 36.8፣ 30.5፣ ሽሬ 37.5፣ 39.9 ተርጫ 48፣ ወገልጤና 40፣ ወረኢሉ 36፣ 46፣ ይትኖራ 38.3፣ ባቱ 67.5፣ አባይ ሸለቆ 32.3፣ 37.1፣ አቦምሪንጋ 44.7፣ 36.9፣ አቃስታ 30.6፣ አንኮበር 35፣ አሺ 32፣ አሸሬ 31.1፣ አሶሳ 30.5፣ አታንጎ 37.7፣ ባምቢስ 45.2፣ ቢላምቢሎ 47.4፣ 33.2፣ 45.2፣ ጨፌዶንሳ 30.7፣ ደበረ ሲና 39.9፣ 80.2፣ 35.1፣ ደጋን 39.8፣ 62.1፣ ደነባ 30.3፣ ደንጎለታ 32.1፣ እርብቲ 47.9፣ ጋሸና 60.7፣ ጊናገር 36.4፣ ጊሽራቤል 45.2፣ ጉብቲ 47.8፣ ጉጉፍቱ 30.2፣ 36.8፣ 39.6፣ 75.5፣ ጉንዶ በረት 46፣ 30፣ ሐገረ ሰላም 36፣ ሃይቅ 78.8፣ ሃሮ 30.4፣ 30.5፣ 40.6፣ ከሚሴ 50.5፣ ቅዳሜ ገቤ 56.4፣ ኩልመስክ 37.7፣ 30.2፣ ማርዬ 51፣ 83.1፣ ሞላሊ 48.7፣ ኦሞናዳ 32.5፣ 30.5፣ ስቆጣ 35.4፣ ሲቦ 45.3፣ ተርኮዲ 38.2፣ ትንሹሜጢ 37.2፣ ጽግሬዳ 31.3፣ መንደር13 32.4፣ 32፣ 30.2፣ ወልዲያ 30፣ ዉቅሮ 63፣ እንዲሁም ገምቢ 46.9 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል። በአጠቃላይ ባለፉት አስራ አንድ ቀናት በ95 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብና ሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 50.5-90 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ60 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካከል ላሊበላ፣ ማርዬ ደብረ ሲና፣ ፉኙዶ፣ ሃይቅ፣ ጉጉፍቱ፣ ቡለን፣ ባቱ፣ ባቲ፣ ዉቅሮ፣ አሶሳ፣ ደጋን፣ ባህርዳር፣ ጭፍራ፣ ጋሸና፣ ማንኩሽ፣ ጨፋ ይገኙበታል፡፡

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ሸገር ከተማ፣ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉና ደቡብ ጎንደር፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ አዊ፣ የደቡብ እና የሰሜን ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉ፣ ምስራቅ እና ደቡብ ምስራቅ ትግራይ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ልዩ ወረዳ፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዠንግ፣ ኑዌር እና ኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ሸካ፣ ቤንች ሸኮ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳዉሮ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ሀዲያ፣ የም፣ ስልጤ፣ ሃላባ፣ ከምባታ ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ፣ አዲስ አበባ ላይ ከ31-220 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ3-11 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ሸገር ከተማ፣ አርሲ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ዞኖች፣ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉና ደቡብ ጎንደር፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ አዊ፣ የደቡብ እና የሰሜን ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉ፣ ምስራቅና ደቡብ ምስራቅ ትግራይ ዞኖች፣ ከአፋር ክልል ሁሉም ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ልዩ ወረዳ፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዠንግ፣ ኑዌር እና ኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ሸካ፣ ቤንች ሸኮ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ሀዲያ፣ የም፣ ስልጤ፣ ሃላባ፣ ከምባታ ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ፣ ጎፋ፣ ባስኬቶ ደቡብ ኦሞ ዞኖች፣ አዲስ አበባ በአብዛኛ መደበኛ እና በጥቂት ቦታዎቻቸዉ ላይ ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡



ካርታ 1 እ.ኤ.አ ጁላይ 21 እስከ 31/2026 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2 እ.ኤ.አ ጁላይ 21 እስከ 31/2026 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት



ካርታ 3 እ.ኤ.አ ጁላይ 21 እስከ 31/2026 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

1.2 እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች ብዙ ቦታዎችን ያደረሰ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸዉ፡፡ ይህም ሁኔታ በጁላይ ወር መጨረሻ ለሚዘሩ የአጭር ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራትና፣ ከኤፕሪል ወር ጀምሮ ለተዘሩ እንደ በቆሎና ማሽላ ለመሳሰሉት የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎችና የጓሮ አትክልቶች የውሃ ፍላጎታቸውን ከሚሟላት አንፃር የጎላ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በሌላ በኩል በምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የነበረው እርጥበት ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የመጠጥ የውሃ ፍላጎትን ለማሻሻል፣ ለግጦሽ ሳርና ለአረንጓዴ እፅዋት ልምላሜ አዎንታዊ ሚና ነበረው (ካርታ 4)።

1.3 እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናት በአብዛኛው ባሮ አኮቦ፣ አባይ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ተከዜ፣ አዋሽ፣ አፋር፣ ደናክል፣ የላይኛውና መካከለኛ ስምጥ ሸለቆ እንዲሁም የላይኛው ዋቢ ሸበሌና ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በላይኛው ኦሞ ጊቤና አባይ ተፋሰሶች ደግሞ በጣም ከፍተኛ የሆነ የገፀ ምድር የውኃ ይዘት ነበራቸው፡፡ ይህም ሁኔታ የገፀ ምድር የውኃ ሃብት ግብዓትን በማሻሻል ወደ ግድቦችና የወኃ ማጠራቀሚያዎች የሚገባውን የውኃ መጠን በመጨመር ረገድ አዎንታዊ አስተዋፅዖ እንደነበረው የተተነተኑ የውኃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 5)።

Ethiopian Meteorology Institute

ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et



ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2026 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2026 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

Ethiopian Meteorology Institute

2. መግቢያ

በመደበኛ ሁኔታ የክረምት ዝናብ ቀደም ብሎ በደቡብ ምዕራብ እና ምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚጀምር ሲሆን፤ በሂደትም እየተጠናከሩ ከሚሄዱ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ጋር ተያይዞ በኦገስት ወር ውስጥ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ሙሉ በሙሉ ዝናብ ያገኛሉ፡፡ የኦገስት ወር ከተቀሩት የክረምት ወራት በተሻለ ሁኔታ ሁሉንም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን አካቶ በመጠንም ሆነ በሥርጭት ከፍተኛ ደረጃ የሚደርስበት ወር ነው። ስለሆነም የወሩ አማካይ የዝናብ መጠን በምዕራብ አጋማሽ በአብዛኛው የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ ከ200-400 ሚ.ሜ እና በአንዳንድ ሥፍራዎች ላይ ከ400 ሚ.ሜ በላይ ይደርሳል። በእነዚህ አካባቢዎች የዝናብ ቀናትም በዚያው መልክ የሚጨምር በመሆኑ ከ18-30 ለሚደርሱት ቀናት ዝናብ ይኖራል። በሌላ በኩል በምስራቅ፣ በሰሜን ምስራቅ እና በመካከለኛው ኢትዮጵያ አካባቢዎች ላይም ቢሆን የዝናቡ መጠንና ሥርጭት እየተስፋፋ የሚሄድ በመሆኑ ከ6-20 ቀናት ያህል እስከ 300 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ በአማካይ ይኖራል።

በመደበኛ ሁኔታ በኦገስት የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኛዎቹ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በይበልጥ ይጠናከራሉ፡፡ በመሆኑም የክረምቱ ዝናብ በስርጭትም ሆነ በመጠን በተሻለ ሁኔታ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን ላይ ከፍተኛ ጥንካሬ የሚያሳይበት ጊዜ ሲሆን በተለይም በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ እና መካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ነጎድጓዳማ እና ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ይዘወተራል፡፡

2.1 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በኦገስት የመጀመሪያው አስር ቀናት ለክረምት ዝናብ መፈጠር ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ይበልጥ እየተስፋፉና እየተጠናከሩ ይሄዳሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን፣ መካከለኛው፣ ምስራቅ እና ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ሥርጭት እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6)። ስለሆነም እርጥበታማው የአየር ሁኔታ በተለይም በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ እና መካከለኛዉ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ በመጠንም ሆነ በሥርጭት እየተስፋፋ ከመሄዱ ጋር ተያይዞ በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል፡፡ በተጨማሪም በደቡብ ምዕራብ፣ ሰሜን ምስራቅ፣ ምስራቅ እና በደቡብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 6 እና 7)፡፡ በሌላ በኩል በመካከለኛው፣ በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ እና ሰሜን ምስራቅ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል የሚችል ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡



ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኦገስት 1-10/2026,
የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

2.2 የሚኖረው የዝናብ ሁኔታ

በሚቀጥሉት አስር ቀናቶች ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አከባቢዎች ብዙ ቦታዎቻቸውን የሚሸፍን ከመካከለኛ እስከ ከባድ (ከ11-30 ሚ.ሜ) መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም በውሃ አካላትና በከባቢ አየር ውስጥ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በመካከለኛው፣ ደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ውስጥ ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል የሚችል ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 7) ፡፡



ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከኦገስት 1-10, 2026 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን

ሠንጠረዠ 1፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና በ24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን

ክልል	ዞን	በ 24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን
ኦሮሚያ	ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፤ ጅማ፣ ምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ሸገር ሲቲ እና ሁሉም የሸዋ ዞኖች	ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ በላይ)
	ምስራቅ እና ምዕራብ ሐረርጌ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ እና ጥቂት የምስራቅ ቦረና ዞን	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ)
አማራ	የምዕራብ፣ መካከለኛ፣ ደቡብ እና ሰሜን ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ የምዕራብ እና የምስራቅ ጎጃም፣ የአዊ ዞኖች	ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ)
	ዋግህምራ፣ የደቡብ እና ሰሜን ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች እና የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፤	ከቀላል እስከ ከባድ መጠን (ከ1-30 ሚ.ሜ)

ጋምቤላ	አኝዋክ፣ መዠንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ	ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ በላይ)
ቤንሻንጉል ጉምዝ	ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች	ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ)
ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ	ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ፣ ምዕራብ ኦሞ	ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ)
ማዕከላዊ ኢትዮጵያ	ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ	ከቀላል እስከ ከባድ መጠን (ከ1-30 ሚ.ሜ)
አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ		ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ)
ትግራይ	የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛው፣ ምስራቅ፣ ደቡብ ምስራቅ እና ደቡብ ትግራይ ዞኖች	ከቀላል እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ)
አፋር	የፋንቲ፣ አዉሲ፣ ማሂ፣ ሀሪ እና ጋቢ ዞኖች	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ)
ሲዳማ ክልል	ሁሉም የክልሉ ዞኖች	ከቀላል መጠን እስከ ከባድ መጠን (ከ1-30 ሚ.ሜ)
ደቡብ ኢትዮጵያ	ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ ኮሬ፣ ባስኬቶ እና ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ዞኖች	ከቀላል መጠን እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ)
ሶማሌ	ሲቲ እና ፋፈን ዞኖች	ከቀላል መጠን እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ)

2.3 የሚኖረው የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት ሁኔታ

በኦገስት የመጀመሪያው አስር ቀናት ከሚኖረው የቀኑ ከፍተኛ የፀሐይ ሀይል ጋር በተያያዘ የቀኑ ከፍተኛ ሙቀት በኤሊ ዳር፣ ዱብቲ፣ ሰመራ፣ ቡሬ፣ አሳይታ፣ ሁንዱፎ፣ ገዋኔ፣ ሚሌ፣ ዳሊፋጊ፣ አይሻ፣ ጉሊና፣ አዋሽ አርባ፣ ባቲ፣ ዶሎ ኦዶ፣ ዳዋ፣ ጎዴ፣ አቦቦ፣ ቋራ፣ አዋሽ ፈንታሌ፣ ጭፍራ፣ ላሬ፣ መተሃራ እና ፉኙዶ አከባበዎች ላይ ከ26 እስከ 38 ዲግሪ ሴልሺየስ እንደሚሆን አሃዛዊ ትንበያዎች ያመላክታሉ (ካርታ 8) ፡፡



ካርታ 8 እ.ኤ.አ. ከኦገስት 1-10, 2025, የሚኖረዉ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ

2.4 እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በኦገስት ሁለተኛዉ አስር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከቀዳሚው አሥር ቀናት በበለጠ ሁኔታ እየተጠናከሩ የሚሄዱበት ጊዜ ነው፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች በአንዳንድ ቦታዎች ላይ በረዶ የቀላቀለ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ለወንዞች ሙላትና ለቅጽበታዊ ጎርፍ መከሰት አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡

በመጪዎቹ የኦገስት ሁለተኛው አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ሥርጭት እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከዚሁ ጋር በተያዘም በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን፣ እና መካከለኛው የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር የአህዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በተጨማሪም በሰሜን ምስራቅ እና ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 9)፡፡



ካርታ 9 እ.ኤ.አ. ከኦገስት 11-20/2026, የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

2.5 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ እና መካከለኛዉ የሀገራችን አከባቢዎች በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው እርጥበት ያገኛ፡፡ በተለይም በደቡብ ምዕራብ፣ ሰሜን ምስራቅ፣ ምስራቅ እና ደቡብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው የአፈር ዉስጥ እርጥበት ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም የሚኖሩ መልካም አጋጣሚዎችን ለመጠቀምና የሚጠበቁ አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ለመቀነስ ከታች የቀረቡትን ቦታ ተኮር የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳብ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል (ሠንጠረዥ 2) ፡፡

2.6 እ.አ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውሀ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሃገራችን ተፋሰሶች ላይ ከመካከለኛ እስከ በጣም ከፍተኛ መጠን የሚደረስ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ይኖራቸዋል። በመሆኑም የሚመለከታቸው የዘርፉ አካላት የሚኖሩ መልካም ዕድሎች በአግባቡ ለመጠቀምና አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ማለትም የጎርፍ መጥለቅለቅ፣ የመሬት መንሸራተት እንዲሁም የደራሽ ወንዝ ሙላትና ሌሎች ተያያዥ የተፈጥሮ አደጋዎች ለመቀነስ የሚከተሉትን ተፋሰስ ተኮር የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች ማከናን ያስፈልጋል (ሠንጠረዥ 3) ፡፡

Ethiopian Meteorology Institute

ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

የክረምት ዝናብ ተጠቃሚና የመኸር ሰብል አብቃይ እንዲሁም አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች			
ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት የሚያገኙ ዞኖች	**አዎንታዊ ተጽዕኖ**	**አሉታዊ ተጽዕኖ**	**የተሰጠ ምክረ ሃሳብ**
ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ሸገር ሲቲ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ የምዕራብ፣ መካከለኛው፣ ደቡብ እና ሰሜን ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ የምዕራብ እና የምስራቅ ጎጃም፣ አዊ ፣አኝዋክ፣ መዠንግ፣ ኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ፣ ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፣ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ	➢ የአፈር ዉስጥ እርጥበት መሻሻል ➢ ለረጅም ጊዜ ሰብሎች እድገት እና ➢ የመኸር ሰብሎች ባልተዘሩባቸዉ አካባቢዎች የአጭር ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራት ➢ ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል ➢ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የውሃ ማጠራቀሚያዎችን ለማጎልበት ➢ ለከተማ ግብርና ስራዎች ➢ ለቋሚ ተክሎች እድገትና ለአረንጓዴ አሻራ መረሃ ግብሮች	➢ የእርጥበት መብዛት፣ የማሳዎች መጨቀየት ➢ ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎች የውኃ በማሳዎች ላይ መተኛት ➢ ውሃገብ በሆኑና በወንዝ ዳርቻ ባሉ ሰብሎች ላይ የአፈር መታጠብ ➢ ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎ ች የመሬት መንሸራተት ➢ የአረም መስፋፋት ➢ የሰብል በሽታና ተባይ መከሰት	➢ የሚገኘውን እርጥበት በመጠቀም ዘግይተዉ የሚዘሩ የመኸር ሰብሎችን መዝራት ➢ ተዳፋታማ ማሳዎች ላይ የተዘጉ የማፋሰሻና የማንጣፈፊያ ቦዮችን ማስተካከል ➢ የሰብል በሽታንና አረምን አስቀድሞ መከላከል፤ ➢ የአፈር መሸርሸር መከላከል ስራዎችን በስፋት መስራት ➢ የመሬት መንሸራተት ተጋላጭነትን መቀነስ ➢ እርጥበት አጠር አካባቢዎች የዝናብ ውሃን ማሰባሰብና ማጠራቀም ➢ የማዳበሪያ አጠቃቀምን በትክክለኛው ሰዓትና የአየር ሁኔታ ምቹነትን ባገናዘበ ሁኔታ መተግበር ➢ አረምን በወቅቱ ማረም፣ ፀረ-አረምና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ከግብርና ባለሙያ ጋር በመመካከር መተግበር

ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት የሚያገኙ ዞኖች	አዎንታዊ ተጽዕኖ	አሉታዊ ተጽዕኖ	የተሰጠ ምክረ ሃሳብ
ምስራቅ እና ምዕራብ ሐረርጌ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ፣ ጥቂት የምስራቅ ቦረና ዞን፣ ዋግህምራ፣ የደቡብ እና ሰሜን ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ፣ የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፣ ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ማረቆ ልዩ ወረዳ፣ የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉ ምስራቅ፣ ደቡብ ምስራቅ እና ደቡብ ትግራይ ዞኖች፣ ፋንቲ፣ አዉሲ፣ ማሂ፣ ሀሪ እና ጋቢ ዞኖች፣ ሲዳማ ሁሉም የክልሉ ዞኖች፣ ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ ኮሬ፣ ባስኬቶ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ሲቲ እና ፋፈን ዞኖች	➢ ሰብሎች ባልተዘሩባቸዉ አካባቢዎች የሚገኘዉን እርጥበት በመጠቀም የመኽር ሰብሎችን ለመዝራት ምቹነት ➢ የአረንጓዴ እፅዋት ልምላሜ፣ ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሣር አቅርቦት መሻሻል ➢ የዝናብ ውሃን ለማሰባሰብና ለማጠራቀም ➢ ለከተማ አካባቢ ግብርና ስራ	➢ የዝናብ መቆራረጥና ደረቅ ሰሞናት መኖር ➢ የትነት መጠን መጨመር፤ ➢ የሰብል በሽታ መከሰት፤ ➢ በተወሰኑ ቦታዎች ላይ የአፈር ውስጥ እርጥበት ዝቅተኛ መሆንና ለሰብሎች የውሃ ፍላጎት በቂ አለመሆን	➢ የሚገኘዉን እርጥበት በቂ መሆኑን በማረጋገጥ ዘግይተዉ የሚዘሩ የመኽር ሰብሎችን መዝራት ➢ የዝናብ ውኃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል ➢ የአፈር ውስጥ የትነት መጠኝን ለመቀነስ የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናወን፤ ➢ የአፈርና ውሃ እቀባ ስራ ማከናወን፤ ➢ የእንስሳት ግጦሽ ሣር በአግባቡ መጠቀምና መጠበቅ፤

Ethiopian Meteorology Institute

ሠንጠረዥ 3 በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሀዉ ዘር ላይ ሊኖር የሚችለው ተጽዕኖ

ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት	አዎንታዊ ተጽዕኖ	አሉታዊ ተጽዕኖ	የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ
• አብዛኛው አባይ፣ ባሮ አኮቦ፣ ተከዜ፣ መረብ በላኛዉና መካከለኛው ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ አዋሽ፣ በላኛዉ የገናሌ ዳዋ	• የገጸ ምድርና የወንዞች ውሃ መጠን መጨመር። • የከርሰ ምድር ውሃ ይዘት መሻሻል። • ለመስኖና ለኃይል ማመንጫ የሚውሉ ግድቦች የውሃ ክምችት መጨመር። • የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል። • የውሃ ኃይል ምርታማነት መጨመርና መሻሻል። • በደረቅ ወቅት የወንዞች መሠረታዊ ፍሰት መጠናከር። • የውሃ ሀብት ተደራሽነትና የአካባቢ ኢኮኖሚ መሻሻል።	• ቅፅበታዊ ጎርፍ መከሰት • የደለል ስጋት መጨመር • የውሃ ብክለት መጨመር • የውሃ ማፋሰሻ ቱቦዎች በቆሻሻ መዘጋት	• ወራጅ ውኃን በእግርም ሆነ በቀላል ተሽከርካሪ ለማቋረጥ አለመሞከር • የዝናብ ውኃ ማሰባሰብና ማጠራቀም • የመጠጥ ውሃን አክሞ መጠቀም • ትንበያዎችንና ምክረ ሀሳቦችን በየጊዜው መከታተል • የፍሳሽ መውረጃ ቦዮችን ማፅዳት • የጎርፍ መቀለበሻ ቦዮችን ማዘጋጀት
ከቀላል እስከ መካከለኛ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት	**አዎንታዊ ተጽዕኖ**	**አሉታዊ ተጽዕኖ**	**የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ**
• የታችኛው አዋሽ፣ አፋር ደናክል፣ አይሻ፣ የላይኛው ዋቢ ሸበሌና የባሮ አኮቦ ተፋሰሶች	• የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት በመጠኑ መሻሻል • የጎርፍም ሆነ የደለል ስጋት መቀነስ	• ከፍተኛ ትነት • እርጥበት አጠር በሆኑ አካባቢዎች መጠነኛ የውሃ እጥረት	• የሚገኘውን የዝናብ ውኃ አክሞ መጠቀም • ወራጅ የዝናብ ውኃን ማሰባሰብና ማጠራቀም • ከቤት ጣራ ላይ ውኃ የመሰባሰብና ማጠራቀም ስራዎች • የአየር ሁኔታ መረጃን በቅርበት መከታተል
ደረቅ የአየር ሁኔታ	**አዎንታዊ ተጽዕኖ**	**አሉታዊ ተጽዕኖ**	**የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ**
ኦጋዴን፣ የመካከለኛውና ታችኛው ዋቤ ሸበሌ እንዲሁም የገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች	• የጎርፍም ሆነ የደለል ስጋት አለመኖር፣	• የትነት መጠን መጨመር	የሚገኘውን ውኃ በቁጠባና በአግባቡ መጠቀም • የገጸ ምድር የውኃ ሀብትን በአግባቡ መያዝ